





PreK-3 Cross District Coalition

# ህጻናት ኪንደርጋርተን ከመግባታቸው በፊት የሚያስፈልጉ መመሪያዎች (AMHARIC)

ወላጆችና ሌሎች የቤተሰብ አባላት የህጻናት የመጀመሪያ መመህራን እንደመሆናቸው መጠን ብህፃናቱ ዕድገት ላይ የሚጫወቱት ሚና በጣም አስፈላጊ ነው። ህፃናት በተለያየ መንገድና ፍጥነት ይማራሉ።ስለዚህ ትምህርት ቤት ሲጀምሩ የተለያየ ችሎታ ይዘው ይመጣሉ ማለት ነው። እነዚህ ከታች የተዘረዘሩት መመሪያዎች ህፃናት ኪንደርጋርተን ለመግባት ወይም ትምህርት ለመጀመር ሲዘጋጁ ሊኖሩዋቸው የሚገባ አንዳንድ ችሎታዎችን ያሳያሉ። ዝርዝሩ የሚያሳየው ወላጆች ልጆቻቸውን ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያመለክታል።


| | ማህበራዊ ግንኙነት/ስሜት | ይህንን ለመስራት በሂደት ላይ ነው/ነች | አዎን፡ ይህንን ስራ በደንድ ያከናውናል |
|---|---|---|---|
| 1 | ልጁ ሁለት ተከታታይ መመሪያዎችን በደንብ ማከናወን ይችላል/ትችላለች እንደዚሁም ሶስት ተከታታይ መመሪያዎችን ማከናወን ጀምረዋል/ጀምራለች። | | |
| 2 | ልጁ በልምድ የሚደረጉትን ነገሮች በማስታወስ ማከናወን ይችላል/ትችላለች/ (ለምሳሌ: እራት፣ገላ መታጠብ፣ጥርስ ማጠብ፣የመኝታ ተረትና ወደ መኝታ መሄድ). | | |
| 3 | ልጁ የሚሰማውን/የሚሰማትን መናገር ይችላል/ትችላለች (ለምሳሌ: ደስ ብሎኛል፣ ደስ አላለኝም፣ ጓጉቻለሁ) ብሎ የመናገርን ችሎታ።   | | |
| 4 | ልጁ ሲናደድ/ስትናደድ ራሱን/ራሷን ማረጋጋት ይችላል/ትችላለች። | | |
| 5 | ልጁ ጃኬቱን/ጃኬትዋን ራሱ/ራሷ መልበስ ይችላል/ትችላለች።  | | |
| 6 | ልጁ ራሱን/ራሷን ችሎ/ችላ ሽንት ቤት መጠቀም ይችላል/ትችላለች።  | | |
| 7 | ልጁ እጁን/እጅዋን መታጠብ ይችላል/ትችላለች። | | |
| 8 | ልጁ የተጠቀመባቸውን አሻንጉሊቶች በየቦታቸው ማስቀመጥ፣ የፈሰሱ አነስተኛ ነገሮችን ማጽዳትና የወደቁትን አነስተና ነገሮች ያነሳል/ታነሳች።  | | |
| 9 | ልጁ ሌሎችን ያካፍላል፣ ተራ ይሰጣል/ይጠብቃል/ትጠብቃለች ሌሎችንም ይረዳል/ትረዳለች።  | | |
| 10 | ልጁ ለሚያጋጥሙት አዲስ ሁኔታዎች ወይም የማያውቃቸው ሰዎች ሲያጋጥሙት/ሟት ማስተካከያ/ለውጥ ያደርጋል/ታደርጋለች። | | |
| 11 | ልጁ ከሌሎች ጋር ተግባብቶ/ታ ይጫወታል/ትጫወታለች። | | |
| 12 | ልጁ ሌሎችን ያባብላል/ታባብላለች። | | |
| 13 | ልጁ እኩያው/ዋ ከሆኑት ልጆች ጋር በየጊዜው የመጫወት ዕድል አለው። | | |

| | አከላዊ | ይህንን ለመስራት በሂደት ላይ ነው/ነች | አዎን፡ ይህንን ስራ በደንድ ያከናውናል |
|---|---|---|---|
| 1 | ልጁ መሮጥ፣ መዝለልና እንደመጋለብ ይችላል/ትችላለች። | | |
| 2 | ልጁ በአንድ እግሩ/ዋ መቆም ይችላል/ትችላለች። | | |
| 3 | ልጁ ትልቅ ኳስ መወርወርና መቅለብ ይችላል/ትችላለች።  | | |
| 4 | ልጁ ኳስ መለጋት ይችላል/ትችላለች። | | |
| 5 | ልጁ በመቀስ መቁረጥ ይችላል/ትችላለች።  | | |
| 6 | ልጁ የእርሳስ አያያዝንና አጠቃቀምን ይችላል/ትችላለች። | | |
| 7 | ልጁ የልብሱን ቁልፍ የመፍታትና የመቆለፍ፣ ዚፑን መፍታትና መቆለፍ ይችላል/ትችላለች።    | | |

| | ቋንቋ | ይህንን ለመስራት በሂደት ላይ ነው/ነች | አዎን፡ ይህንን ስራ በደንድ ያከናውናል |
|---|---|---|---|
| 1 | ልጁ በቃላት ተጠቅሞ/ማ ሃሳቡን/ሃሳቧን እና ፍላጎቱን/ፍላጎትዋን መግለጽ ይችላል/ትችላለች። | | |
| 2 | ልጁ የሚታወቁትን ነገሮች ስም መሰየምና መግለጽ ይችላል/ትችላለች። | | |
| 3 | ልጁ በየቀኑ አዳዲስ ቃላትን ይጠቀማል/ትጠቀማለች።   | | |
| 4 | ልጁ በጥራት ይናገራል/ትናገራለች፣ የሚናገረውንም/የምትናገረውንም ብዙ ሰዎች ይገባቸዋል። | | |
| 5 | ልጁ ከ4 እስከ ስድስት ቃላት ያለበትን ዓረፍተ-ነገር ይናገራል/ትናገራለች። | | |
| 6 | ልጁ አስቀድመው ስለተፈጸሙት ነገሮች በደንብ አጣርቶ ይናገራል/ትናገራለች። | | |
| 7 | ልጁ ስለ አንድ አርእስት ከሌላ ሰው ጋር ተራውን ጠብቆ/ጠብቃ መወያየት ይችላል/ትችላለች ። | | |

## ኮግኒቲቭ( የስነአእምሮ ዕድገት)

| | ኮግኒቲቭ( የስነአእምሮ ዕድገት) | ይህንን ለመስራት በሂደት ላይ ነው/ነች | አዎ፡ ይህንን ስራ በደንድ ያከናውናል |
|---|---|---|---|
| 1 | ልጁ አንድን ፕሮብለም ለመፍታት የተለያየ ዘዴ ይጠቀማል/ትጠቀማለች። | | |
| 2 | ልጁ አንድን ነገር ለማወቅ ያለውን ጉጉት ያሳያል እንዲሁም ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መልስ ይፈልጋል/ትፈልጋለች። | | |
| 3 | ልጁ በጨዋታ ጊዜና ፕሮብለሞችን ለመፍታት የመፍጠርና የተለያዩ ሓሳቦችን የማቅረብ ችሎታ ያሳያል/ታሳያለች። | | |
| 4 | ልጁ የተለያዩ ነገሮችን በቀለም(ከለር)፣በቅርጽና በመጠን ለያይቶ/ታ መስቀመጥ ይችላል/ትችላለች። | | |
| 5 | ልጁ በአንድ ቦታ ለመቀመጥ፣ በጥሞና ማዳመጥና የሚካሄደውን በደንብ መከታተል ይችላል/ትችላለች። | | |



## መጻፍና ማንበብ


| | መጻፍና ማንበብ | ይህንን ለመስራት በሂደት ላይ ነው/ነች | አዎ፡ ይህንን ስራ በደንድ ያከናውናል |
|---|---|---|---|
| 1 | ልጁ ከ 5 እስከ 10 የሚሆኑትን ተመሳሳይነት ያላቸውን ቃላት ወይም የህፃናት መዝሙር ያውቃል/ታውቃለች። | | |
| 2 | ልጁ በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ ቃላትን ለይቶ ያውቃል (ለምሳሌ: big, brown, bear). | | |
| 3 | ልጁ ቃላት በድምጽ ተከፋፍለው ሲነበቡ ያውቃል/ታውቃለች (ለምሳሌ: hap-py, 2 ክፍሎች ወይም 2 አነባብ)። | | |
| 4 | ልጁ ከ10 እስከ 20 የሚሆኑትን ትልልቅ ፊደሎችና ከ10 እስከ 20 የሚሆኑትን ትንንሽ ፊደሎች ለይቶ ያውቃል/ታውቃለች። | | |
| 5 | ልጁ ከ10 እስከ 20 የሚሆኑትን ፊዳላት ድምጻቸውን አስተካክሎ ያነባል/ታነባለች። | | |
| 6 | ልጁ የአንድን መጽሐፍ ክፍሎች ለይቶ ያውቃል/ታውቃለች(ለምሳሌ፡ የመጽሓፉ ሽፋን፣አርእስት ገጾቹና ቃላቶቹን የመሳሰሉ) | | |
| 7 | ልጁ ከአዋቂዎች ጋር ሆኖ በየቀኑ ያነባል፣ የመጽሓፉን ተረት ያዳምጣል፣ይናገራል ተረቱንም ደግሞ ለሌሎች ይነግራል። | | |
| 8 | ልጁ በስዕል ወይም ቃላትን ተጠቅሞ ተረት (ታሪክ) "ይጽፋል/ትጽፋለች"። | | |
| 9 | ልጁ የስሙን/ሟን ፊደሎች በደንብ ለይቶ/ታ በማወቅ ይጽፋል/ትጽፋለች። | | |
| 10 | ልጁ የእንግሊዘኛ ፊደሎችን ያነባል/ታነባለች። | | |













## ሒሳብ

| | ሒሳብ | ይህንን ለመስራት በሂደት ላይ ነው/ነች | አዎ፡ ይህንን ስራ በደንድ ያከናውናል |
|---|---|---|---|
| 1 | ልጁ ከ10 እስከ 20 የሚሆኑትን ዕቃዎች እያመለከተ መቁጠር ይችላል/ትችላለች።። | | |
| 2 | ልጁ ድምጹን/ድምጿን ከፍ በማድረግ እስከ 20 ድረ በቅደም-ተከተል መቁጠር ይችላል/ትችላለች። | | |
| 3 | ልጁ የተለያዩ ነገሮችን በማወዳደር ይበልጣል፣ያንሳል እና እኩል የሚሉትን ቃላት ማወቅ ጀምረዋል/ጀምራለች። | | |
| 4 | ልጁ ከ1 እስከ 10 ያሉትን ቁጥሮች ለይቶ ያውቃል/ታውቃለች። | | |
| 5 | ልጁ የተለያዩ ነገሮችን በመቁጠር ከተጻፉ ቁጥሮች ጋር ያዛምዳል/ታዛምዳለች። | | |
| 6 | ልጁ የተለያየ ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች ይለያል/ትለያለች። (ለምሳሌ: ክብ፣ ባለ ሶስትና ባለ አራት መአዘን ቅርጾችን)(circle, square,triangel,rectangle) | | |
| 7 | ልጁ ቀለል ያለ ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች ይለያል/ትለያለች እንዲሁም ያዛምዳል/ታዛምዳለች። | | |
| 8 | ልጁ የመለኪያ ነገሮችን ይጠቀማል/ትጠቀማለች (ለምሳሌ: ኩባያ፣ ማንኪያ፣ ማስመሪያና መመዘኛ(ሚዛን))። | | |
| 9 | ልጁ የተለያየ መጠን ፣ቅርጽ እና ክብደት ያላቸውን ነገሮች ለመግለጽ በቃላት ይጠቀማል (ለምሳሌ: big, circle, heavy). | | |
| 10 | ልጁ ነገሮችን በቅደም-ተከተል ማስቀመጥ ይችላል/ትችላለች (ለምሳሌ: 1ኛ፡ 2ኛ፡ 3ኛ) | | |








## የግል መረጃ

| | የግል መረጃ | ይህንን ለመስራት በሂደት ላይ ነው/ነች | አዎ፡ ይህንን ስራ በደንድ ያከናውናል |
|---|---|---|---|
| 1 | ልጁ የመጠሪያ ስሙን/ስሟን የመጨረሻ ስሙን/ስሟን እና የወላጆቹን ስም ያውቃል ታውቃለች። | | |
| 2 | ልጁ የመኖሪያ አድራሻውንና ስልክ ቁጥሩን ያውቃል/ታውቃለች። | | |
| 3 | ልጁ 10 የሰውነታችንን ክፍሎች (ለምሳሌ፡ጭንቅላት፣ ትከሻ፣ ጉልበት ጣቶችና የመሳሰሉትን)ያውቃል/ታውቃለች። | | |
| 4 | ልጁ ዕድሜውንና የትውልድ ቀኑን ያውቃል/ታውቃለች። | | |







Developed by the PreK-3 Cross District Coalition of Edmonds, Everett, Federal Way, Highline and Seattle Public Schools. Aligned with Teaching Strategies GOLD, WaKIDS (Washington Kindergarten Inventory of Developing Skills) Progressions of Development & Learning and adapted from Characteristics of Children Entering Kindergarten. Changes will not be made to this document without the written consent of the PreK-3 Cross District Coalition. Funded by the Bill & Melinda Gates Foundation. January 2014.